# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 62 ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም


ወያኔ የሃሰት ምስክሮችን የሚፈልጋቸው የያዘው ጉዳይ እስኪያልቅለት ድረስ ብቻ ነው፡፡ በተቀናቃኞቹ ላይ አስፈርዶ ፋይሉ ከተዘጋለት በኋላ የሃሰት ምስክሮቹን የሚንከባከብበት ምክንያት አይኖረውም፤ እንዲያውም የጎነጎነውን የቅጥፈት ሴራ ደብዛ ለማጥፋት ሲል ራሱ የፈጠራቸውን የሃሰት ምስክሮችን ተከታትሎ የሚያስወግድ መሆኑ ተደጋግሞ የታየው ጉዳይ ነው፡፡

ርዕሰ አንቀጽ

## ዶናልድ ፔይን ፕሬዚዳንት ኦባማ ለአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ጥብቅ ትእዛዝ ማስተላለፍ እንዳለባቸው ተነገሩ

የአሜሪካ የኮንግረስ አባል የሆኑት እውቁ ዶናልድ ፔይን ፕሬዚዳንት ኦባማ ለአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ጥብቅ ትእዛዝ ማስተላለፍ እንዳለባቸው ተነገሩ።

የተከበሩ ሚ/ር ፔይን ለኦል አፍሪካ ድህረ ገጽ እንደገለጹት የአምባገነኑ መለስ አገዛዝ ሕዝቡን ማሰርና ማሰቃየቱን ማቆም አለበት። በአገሪቱ ውስጥ ፍትህ ጠፍቷል፤ ሙስናም ያለቅጥ ተስፋፍቷል ያሉት እውቁ አሜሪካዊ ዲፕሎማት፣ የኦባማ አስተዳደር ለመለስ ዜናዊ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ መላክ እንደሚገባው ተናግረዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ወያኔ ለአገዛዙ ታማኝ አልሆኑም ያላቸውን በርካታ ፖሊሶች አባረረ

ተስፋ እየቆረጠ የመጣው ያምባገነኑና ዘረኛው የመለስ ቡድን፣ ለአገዛዙ ታማኝ አልሆኑም ያላቸውን በርካታ ፖሊሶች አባረረ።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ ይህን እርምጃ የወሰደው ከሁለት ወራት በፊት በርካታ የአዲስ አባባን ፖሊሶች በጦላይ ወታደራዊ ካምፕ ሰብስቦ ለአገዛዙ ያላቸውን የፖለቲካ ታማኝነት እንዲያሳውቁ ከጠየቀ በሁዋላ ሲሆን፣ “ፖሊስ ገለልተኛ ነው” የሚል አቋም ያራመዱ ከ500 የማያንሱ ፖሊሶች እንዲባረሩ ተደርገዋል። ፖሊሶቹ የተባረሩት የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን ትደግፋላችሁ፣ ከግንቦት 7 ንቅናቄም ጋር ግንኙነት አላችው በሚል ሰበብ ሲሆን፣ ፖሊሶቹ ግን ታማኝነታችን ለህዝብ እንጅ ለማንም የፖለቲካ ድርጅት አይደለም የሚል ጠንካራና አገዛዙን ያስደነገጠ መልስ መስጠታቸው ታውቋል።

አገዛዙ ከጊዜ ወደ ጊዜ አገሪቱን መግዛት እየተሳነው በመምጣቱ፣ ፖሊሶችንና የመከላከያ አባሉትን እየተጠራጠረ እንደሚገኝ የሚናገሩት የፖሊስ አባላት፣ ድንጋጤ በተፈጠረበት ቁጥር ፖሊሶችና ወታደሮች እየተሰበሰቡ ታማኝነታቸውን ላገዛዙ እንዲገልጹ እንደሚደረጉ እኚሁ አባላት ተናግረዋል። ከጥቂት የትግራይ ተወላጅ ፖሊሶች ውጭ ያለው ፖሊስ ሁሉ ከወያኔ ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑን የሚናገሩት ፖሊሶቹ፣ በርካቶቹ በእየጊዜው ስራውን እየለቀቁ በመጥፋት ላይ መሆናቸውንም አክለዋል።

በፖሊሶች መጥፋት የተበሳጨው የወያኔ አገዛዝ፣ ማንኛውም የፌደራል ፖሊስ አባል ታድኖ እንዲያዝ ደብዳቤ በተለያዩ ቀበሌዎች መበተኑን መዘገባችን ይታወሳል። ይህን ደብዳቤ ተከትሎም በርካታ የፖሊስ አባላት እየተያዙ መታሰራቸውን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ወያኔ የሃሰት ምስክሮችን ሚስጥር ያወጣሉ በሚል ስጋት ያስገድላል

የቀድሞው የመላው አማራ ህዝብ ፕሬዚደንት በነበሩት በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ላይ በወያኔ ተደልለው በሃሰት ከመሰከሩት ሶስት የጎጃም አርሶ አደሮች መሃል ሁለቱ ምስጢር ያወጣሉ በሚል ስጋት በወያኔ ታጣቂዎች መገደላቸው ታወቀ፡፡

አስተማማኝ ከሆኑ የወያኔ የደህንንት ምንጮች ግንቦት-7 ንቅናቄ የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ወያኔ በፕሮፉሰር አስራት ወልደየስ ላይ ካቀረባቸው በርካታ የሃሰት ምስክሮች መሃል ሶስቱ የጎጃም አርሶ አደሮች ነበሩ፡፡ እነኚሁ የደህንነት ምንጮቻችን አርሶ አደሮቹ በሃሰት ከመሰከሩ በኋላ ልብስ ተገዝቶላቸውና የገንዘብ ስጦታ ተደርጎላቸው ወደ መጡበት እንዲመለሱ መደረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

ምንጮቹ አጠናቅረው ለግንቦት 7 የላኩት መረጃ፡- ‹‹…ይሁንና አርሶ አደሮቹ በፕሮፌስር አስራት ላይ ወያኔ የሸረበውን የግፍ ሴራና የሀሰት ምስክርነታቸውን ሚስጥር በሆነ አጋጣሚ ሊያወጡ ይችላሉ ተብሎ በመሰጋቱ-ምስክርነታቸውን ሰጥተው ወደ ጎጃም በተመለሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተገድለዋል” ይላል።

መረጃው አገዳደላቸውንም ሲያብራራ፡-አንዱ አርሶ አደር በእርሻ ስራ ላይ እንደነበር በገዛ ማሳው ውስጥ፤ ሌላው ደግሞ በሚኖርበት መንደር መንገድ ላይ በጠረራ ጸሃይ የተገደሉ መሆናቸውን ከጠቀሰ በሁዋላ፡- “ሶስተኛው አርሶ አደር ግን እስካሁን የደረሰበት አይታወቅም” ብሏል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ መታሰር በርካታ የብአዴን አባላትን አስቆጣ የተቀሰቀሰው የነፃነት ትግል ወደ አህዴድም ተሸጋገረ

እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ ቢታሰሩም እልፍ ተፈራዎች ተወልደናል ሲሉ የብአዴን አባላት ተናገሩ። በብአዴን ውስጥ የተቀሰቀሰው የነፃነት ትግል ወደ ኦህዴድም መሸጋገሩ ታወቀ።

የመለስን ቡድን ዘረኛነት በመቃወም “የአማራ ህዝብና የብአዴን አባላት ከወያኔ የግፍ አገዛዝ ነጻ መውጣት ይገባቸዋል” በማለት ለረጅም ግዜ ትግል በማደረግ የሚታወቁት ጄነራል ተፈራ ማሞ ለእስር ቢዳረጉም በአማራ ህብረተሰብ ውስጥ የተቀሰቀሰው ”እምቢ ለወያኔ” ትግል አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉ ታወቀ፡፡ ትግሉ ወደ ኦህዴድም መሸጋገሩ ተሰማ።

የግንቦት 7 ውስጣዊ ምንጮች እንዳሉት የነፃነት ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ በህብረተሰቡ፤ በብአዴን አበላት እና በሰራዊቱ ውስጥ በሚገኙ ነፃነት ወዳዶች አማካይነት እየተቀጣጠለ ነው። በተለይ የብአዴን አባላት በስፋትና በእልህ በአንድ ልብ መቆማቸው የታወቀ ሲሆን፤ የነጀነራል ተፈራ ማሞ መታሰር -ይበልጥ ለትግል ያነሳሳቸው ካልሆነ በቀር ከዐላማቸው ሊመልሳቸው እንደማይችል ብዙዎቹ እያረጋገጡ ይገኛሉ።

“የ ትግል መሪዎችን በማሰር ትግልን ማዳከም ይቻላል “ብሎ ማሰብ ኢህአዴግም ሆነ አባል የሆንንበት ብአዴን መሪዎች፤ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሲያራምዱት የቆየ ደካማ አስተሳሰብ ነው” ያሉት በርካታ የብአዴን አባላት፤ የነ ጀነራል ተፈራ ማሞ መታሰርም ውስጣዊ ትግሉን ለማኮላሸት ታስቦ በዕቅድ የተፈፀመ ለመሆኑ ቅንጣት አንጠራጠርም ብለዋል።

ሆኖም ዛፍ ሲቆረጥ ከስሩ በርካታ ቁጥቋጦ እንደሚያፈራ ሁሉ የነ ጀነራል ተፈራን መታሰር ተከትሎ እልፍ ተፈራዎች ተወልደናል ያሉት የብአዴን አባላት፤ ከተነሳንበት ዐላማ ጉዞአችንን ያሳተን የዘረኝነት ጀልባ መስጠሙና የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና ፍትህ መቀዳጀቱ የማይቀር የቅርብ እውነት ሆኗል ብለዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በኢትዮጵያ የተፈጠረው የሀይል እጥረት ለወያኔ ሰፊ የሙስና በር ከፍቷል

የኃይል እጥረት የፈጠረው ቀውስ በኢትዮጵያ አኮኖሚ ላይ ዘላቂ ችግር እየፈጠረ ቢሆንም በግለሰብ ደረጃ ለራሱ ለመለሰ እና ለጥቂት ሹመኞቹ ግን ከሰማይ እንደወረደ መና የሚቆጠር ሆኗል ሲሉ አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የአገዛዙ ባለስልጣን አጋለጡ፡፡

ባለስልጣኑ ለግንቦት 7 ድምፅ የሰጡት አጭር ገለፃ- የሀይል እጥረቱን ተከትሎ ከተሞችን ያጥለቀለቁትንና ከትናንሽ እስከ ትላልቅ ጉልበት ያላቸው ጄኔሬተሮችን በማስመጣት በስፋት እየቸበቸቡ ያሉት -አዜብ መስፍንና ሌሎች ጥቂት የወያኔ ባለስጣኖች ናቸው ፡፡ ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የውያኔ ሹመኞች በየሄዱበት አገር መክዳት የአገዛዙ የመጨርሻ ሰዓት መድረሱን አመላካች ነው

የመለስ ሹመኞች ለስራ ጉዳይ በሚሄዱባቸው የውጭ አገሮች ድርጅታቸውንና አገራቸውን ጥለው መቅረት መጀመራቸው-አገዛዙ 11ኛው ሰዓት ላይ መሆኑን የሚያመላክት ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ተናገሩ።

በመንግስታ ውድቀት ዋዜማ ከሚታዩት የህመም ምልክቶች አንዱ ምናልባትም ዋነኛው ቁልፍ ባለስልጣኖች ወይም እንደ ምሁራኑ አባባል ‹‹መድፍ ቢተኮስ የአለቃቸውን እጅ አይለቁም›› ተብለው እምነት የተጣለባቸው ሹመኞች በወጡበት መቅረት መጀመራቸው ነው፡፡

የበረከት ስምኦን ምክትል ሆኖ በኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ ተሹሞ የነበረው ኤርምያስ ለገሰ መለስን ‹‹ዞር በል›› ብሎ ከሳምንት በፊት ለስራ ጉዳይ ተብሎ በተላከበት አሜሪካን አገር እንደቀረ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መዘገቡ ይታወሳል።

ይህ ዜና ገና በጆሮ ማንቃጨሉን ሳያቆም እነሆ የቴሌ ኤጀንሲ ዳይሬክተርም ‹‹ኤርምያስን የሚከተሉ ብፁዓን ናቸው›› ብለው ወደ አሜሪካ መኮብለላቸው ተዘግቧል። ዳይሬክተሩ አቶ እሸቱ ዓለሙ በኤክስኪዩቲቭ ቴሌኮም ማኔጅመንት ለ15 ቀናት የሚቆይ ስልጠና ለመሳተፍ ተብለው በተላኩበት አሜሪካ በመቅረት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው ታውቋል።

የአገዛዙን ገመናና ምስጢር የሚያውቁ ከመሆናቸው አንፃር እንደነዚህ ዓይነት ቁልፍ ባለስልጣናት ባልተገመተ ሁኔታ ከአሰቀያሚው ጀልባ ወርደው “በቃኝ” ማለታቸው፤ አገዛዙ የቆመበት መሬት እንደከዳውና ፀንቶ የሚቆምበት ምንም ዓይነት ሕዝባዊ መደላድል እንደሌለው በመገንዘባቸው ነው ይላሉ ምሁራኑ። ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ፍትህን የሚያረክሱትን የወያኔ ቅጠረኞች በቁርጠኛነት እንታገላለን

ፍትህ የነፃነትና የእኩልነት ማረጋገጫ፤ ግለሰቦችና ቡድኖች በሥርዓት እንዲኖሩ ማድረጊያ እና የአንድ ማኅበረሰብ የሞራል እሴቶች ተፈፃሚነት ማረጋገጫ ነች፡፡ ፍትህ በሌለበት ነፃነት፣ እኩልነት፣ ሰላም፣ ልማት እና ዲሞክራሲ ትርጉም የላቸውም፡፡ በፍትህ ላይ ማላገጥ የወንጀሎች ሁሉ ቁንጮ ነው፡፡ ወያኔ ከፓርላማ እስከ ወረዳ ፍርድ ቤቶች በሁሉም ቦታዎችና በሁሉም ጊዜዓት የዘረኛ አገዛዙ መሣሪያ በማድረግ የተከበረችው ፍትህን አርክሷል፡፡ የወያኔን እድሜ ማሳጠር እጅግ አስፈላጊ የሚሆነበት አንዱ ምክንያት ወያኔ በሚኖረው እያንዳንዱ ተጨማሪ ደቂቃ የተከበረችዋን ፍትህን ይበልጥ እያረከሳትም በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

ወያኔ ፍርድ ቤቶችን በፍትህ የማላገጥ ተውኔት የሚታይባቸው ትያትር ቤቶች አድርጓቸዋል መሪ ተዋንያኑ "ምስክሮች"፣ "ዳኞች" እና "አቃቢ-ህግ" በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ተዋንያን የሰሯቸውን አሳፋሪ ተውኔቶችን ከዚህ በፊት ከፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ፣ ከቅንጅት መሪዎች፣ ከኦነግ እና ኦብነግ ጋር በተያያዘ አያሌ ወገኖቻችን ተከሰው በቀረቡባቸው ችሎቶች ላይ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ በእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ እየተደገመ ነው፡፡

በቅርቡ በገንዘብ የተደለሉ እና በፍርሃት የተሸማቀቁ የሃሰት ምስክሮች በእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ጉዳይ ላይ ያላዩትን አየን፣ ያልሰሙትን ሰማን እንዲሉ ተነግሮዓቸው አጥንተው የገቡት እየጠፋቸው ሲርበተበቱ ተስተውለዋል፡፡ በፍርሃትም ሆነ በገንዘብ በመደለል በሃሰት መመስከር ወንጀል ሲሆን፤ በእምነት ረገድ ሲታይ ደግሞ አስነዋሪ ክህደት ነው፡፡ በተለይም የሃሰት ምስክርነቱ የተሰጠው አንድን ዘረኛና አምባገነን ሥርዓትን ለመገርሰስ የሚፋለሙ የሕዝብ ልጆችን ለማጥቃት በተዘጋጀ የፍርድ ተውኔት ውስጥ ሲሆን ደግሞ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ የመሆኑን ያህል አፀፋውም የዚያውኑ ያህል ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል እንላለን፡፡

ወያኔ የሃሰት ምስክሮችን የሚፈልጋቸው የያዘው ጉዳይ እስኪያልቅለት ድረስ ብቻ ነው፡፡ በተቀናቃኞቹ ላይ አስፈርዶ ፋይሉ ከተዘጋለት በኋላ የሃሰት ምስክሮቹን የሚንከባከብበት ምክንያት አይኖረውም፤ እንዲያውም የጎነጎነውን የቅጥፈት ሴራ ደብዛ ለማጥፋት ሲል ራሱ የፈጠራቸውን የሃሰት ምስክሮችን ተከታትሎ የሚያስወግድ መሆኑ ተደጋግሞ የታየው ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በፊት በፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ላይ በሃሰት ከመሰከረቱት ሶስት የጎጃም አርሶ አደሮች ሁለቱን የወያኔ ሰላዮች በአሳቻ ቦታዎች፣ ቀናትና ሁኔታዎች ገድለዋቸዋል፤ ቀሪው የት እንደደረሰ አይታወቅም፡፡

የወያኔ የሃሰት ምስክሮች የሁለት ወገን ሰይፍ ውስጥ መግባታቸውን እንዲያውቁት አበክረን እናስገነዝባለን፡፡ በአንድ በኩል፤ ራሱ ወያኔ ባስጠናቸው መንገድ ከመሰከሩለት በኋላ ያስወግዳቸዋል፡፡ በሌላ በኩል፤ ደግሞ ለነጻነቱ የቆሙትን ልጆቹን ለዘረኛ አምባገነኖች አሳልፈው የሰጡትን ከሃዲዎች ሕዝብ ዝም ብሎ አያያቸውም፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምናስተላልፈው መልእክት የሃሰት ምስክሮችን የወያኔ ቁንጮዎች ከሆኑት ከነመለስ፣ ስብሃትና በረከት ለይተን የማናያቸው መሆኑን ነው፡፡ ክህደታቸውን የሚመጥን ቅጣት እስኪያገኙ ድረስ ሁላችንም ዓይናችንን ከእነሱ ላይ መንቀል የለብንም፡፡

ባርነት ውስጥ ተጠፍረው እያሉ በነጻነት የሚሠሩ በማስመሰል አሳዳሪዎቻቸው የሰጧቸውን ፍርድ ለማጽናት ሲባል የዳኝነትን ስም ብቻ ተሸክመው ፍትህንም የዳኝነት ሙያንም እያረከሱ ያሉ ግለሰቦችም ከተግባራቸው እንዲታቀቡ በጥብቅ እያስጠነቀቅን የወያኔ መጠቀሚያ እንዳይሆኑ መንገድ መፈለግ የራሳቸው ኃላፊነት መሆኑን እንነግራቸዋለን፡፡ የወያኔ አቃቢያነ ህግ ወዮላችሁ! ያላገጣችሁባት ፍትህ እናንተ ባልጠበቃችሁት ሁኔታ፣ ግዜና ቦታ ቁጣዋን ታወርድባችኋለች፡፡

ለፍትህ መቆም ነፃነቱንና አገሩን የሚወድ ዜጋ ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ የወያኔ ምስክሮችን፣ ዳኞችና አቃቤዓነ-ህግ በየደረሱበት ማዋረድ፣ የክህደት ሥራዎቻቸውን መዝግቦ መያዝ፣ በዓይነ ቁራኛ መከታተል የሁላችንም ግዴታ ነው፡፡ በሃሰት ምስክሮች፣ ዳኞችና አቃቢያነ-ህግ ላይ ቁጣችንን የምንገልጽበት ጊዜ ተቃርቧል፡፡ በእነዚህ ህሊናና ወኔ ቢስ አድርባዮች ፍትህ ስትቀበር፣ ዘረኝነት ሲወደስ፣ ታጋዮቻችን ሲገደሉ፣ ሲንገላቱና ሲበደሉ ማየት በቃን ብለናል፡፡ ፍትህን የሚያረክሱትን የወያኔ ቅጠረኞችን በቁርጠኛነት፣ አምርረን እንታገላለን፡፡

## የወያኔ የፍርድ ቤት ትርዒቶችና እንድምታወቻቸው

ተደጋጋሚ የወያኔ ፍርድ ቤት ድራማዎች ተዋንያኑን ፈሪዎች፣ ከሃዲዎችና አድርባዮች ከማድረጉም ባለፈ ሥርዓቱ ራሱ ፈጽሞ እንዲታወር አድርጎታል፡፡ ባሁኑ ሰዓት ወያኔ ከድራማ ውጭ ያለውን እውነተኛ ማንነቱን የሚያይበት አንዳችም እድል የለም፡፡ ይህ ደግሞ ወያኔ መወገድ ካልሆነ በስተቀር መሻሻል የማይችል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉትን በአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ወያኔ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትን አምጥቻለሁ እያለ ያቅራራል፡፡ እውነታው ግን እሱ እንደሚለው አለመሆኑን ለመረዳት ፍርድ ቤቶችንና እስር ቤቶችን መቃኘት በበቃ ነበር፡፡ የወያኔ አቃቤያነ-ህግና ዳኞች የሙብትን ጥያቄ "ህገ-መንግሥቱን በኃይል የመገርሰስ" ወንጀል ብለው፤ በሃሰት አስመስክረው ይፈርዳሉ፡፡ ይህ የወያኔን ዓይንና አዕምሮን ያሳውራል፤ ታጋዮቹ የተነሱበት ጥያቄ ግን ታፍኖ ይቆይ እንደሆን እንጂ አብሮዓቸው አይታሰርም፡፡ በዚህም ምክንት ወያኔ ስለብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ይዘምራል፤ እስር ቤቶች ግን "የብሄር ጭቆና እየደረሰብን ነው" ብለው በተነሱ ታጋዮች ተጨናንቀዋል፡፡ በየጊዜውም እዚህም እዚያም ዘውግን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች እየፈነዳዱ አገሪቷን እያመሱ ነው፡፡

አገር ያወቀውን ሃቅ በመናገሯ ለእድሜ ልክ እስር የተዳረገችው የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይም የፍትህ ሥርዓቱ በትወና መበላሸት አንዱ አመላካች ነው፡፡ የወያኔ "የህግ ተንታኞች" የተሰኙት ተዋንያን ብርቱካን የተናገረችው ህገወጥ ነው ሲሉ ተወኑ፡፡ ይህ ተውኔት እሷን ለዳግም እስርና እንግልት አበቃት፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ግን የቅንጅት መሪዎች በተፈቱ ሰሞን ብርቱካን የሰጠችውን ዓይነት መግለጫ ራሱ መለስ መናገሩን ለማስታወስ የደፈረ ከወያኔ "ምሁራን" አንድም አልተገኘ፡፡ ብርቱካንን በማሰር እውነትን ማሰር እንደማይቻል የሚገነዘብ ሰው በመካከላቸው አለመኖሩ ወገባችንን ጠበቅ፤ ሃሞታችንን መረር እንድናደርግ አድርጎናል፡፡

አሁን ደግሞ ዘረኝነት ያንገፈገፋቸው የሠራዊቱ እና የብአዴን አባላት እንዲሁም ሌሎችንም ዜጎች ተባብረው በዘረኝነት ላይ ሲነሱ የችግሩን ምንጭ አጥንቶ መፍትሄ በመሻት ፋንታ የብሶት መገለጫ የሆኑትን መኮንኖች፣ አዛውንትና ጎልማሶችን አስሮ፣ በበርካታ ወንጀሎች ከሶ እና በሃሰት አስመስክሮ ለእርድ ማቅረብ አሁንም ሌላው የወያኔን ብኩን ተውኔት አካል ነው፡፡

እነዚህ ሶስት ማስረጃዎች የወያኔ የፍርድ ቤት ትርኢቶች ራሱ ወያኔን አሳውሮት እውነተኛ ማንነቱም ማየት አለመቻሉን ይገልፃሉ ብለን እናምናለን፡፡



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 62 ሐምሌ 16 , 2001 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ሃይለ ሀሳብ

## ከወያኔ ዘረኛ እምነቶችና ድርጊቶች ምን እየተማርን ነው። የዘረኛነትን አደጋ ለመታገል ምን ማድረግ እንችላለን?

አንዳርጋቸው ጽጌ (ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓም፣ ሚነሶታ አሜሪካ በግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር)

እያቆሰለንና እያደማን ስለመጣው የወያኔ ዘረኛነት ሁላችንም እናውቃለን። ዝርዝሩን ማቅረብ አያስፈልግም። ይህ ዘረኛነት እያስከተለ ስላለው መዘዝና ሁላችንም ይህንን መርዘኛ መዘዝ ለመታገል ምን ማድረግ እንደሚገባን ጥቂት ከማለቴ በፊት ለመግቢያ ወይም አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ለመዋዣ እንዲሆነን በሚቀጥለው ነጥብ ልጀምር።

ወደ አሜሪካ ጉዞዬን ስጀምር የጉዞ ባልደረባዬ እንዲሆን የመረጥኩት መጽሃፍ የታዋቂውን ሩሲያዊ የፈዮዶር ዶስቶቭስኪ ዘ ብራዘርስ ካራማዞቭ የተሰኘውን መጽሃፍ ነበር።

የኔ ትውልድ እንዲህ አይነቶቹን መጽሃፍት የማንበብ ልምድ የነበረው ቢሆንም እያደር እንደተረዳሁት እነዚህን መጽሃፍት ያነበብንበት እድሜያችን፤ የህይወት ተመክሮአችን፣ ያነበብነበት የአእምሮ ቅላጼ/mind set፣ የቋንቋ ችሎታችን ደካማነትና ሌሎችም ነገሮች በአንድ ላይ ተደምረው፤ የእነዚህን ድንቅ ስነጽሁፎች ለዛና ውበት አጣጥመንና መልክቶቻቸውንም ተረድተነው ነበር የሚል እምነት እንዳይኖረኝ አድርገውኛል። በእዚህ የተነሳ ከቅርብ ግዜ ወዲህ እነዚህን መጽሃፍት እንደገና ማንበብ ጀምሪያለሁ። እየገረመኝ ያለው ነገር በወጣትነት እድሜ ያላየሁዋቸው በርካታ ቁም ነገሮች በእነዚህ መጽሃፍት ውስጥ ማየት መጀመሬ ነው። ታላላቆቼ ‹‹ህይወት ትምህርቱ የማያልቅበት ዩኒቨርስቲ ነው›› ሲሉ እየሰማሁ በማደጌ በልጅነት ድንቁርናዬ መገረም የለብኝም።

ዶስቶቭስሲ ዘ ብራዘርስ ካራማዞቭ በተሰኘው መጽሃፉ ውስጥ አባ ዞሲማ የተባሉትን አረጋዊ ገጸ ባህርይ፤ አንደበቱ አድርጎ ‹‹ገሀነብ ምንድነው››? የሚል ጥያቄ አንስቶ ምላሹን በእኚሁ መንፈሳዊ ሰው አንደበት ሲመልስ እንዲህ ብሎናል።

‹‹ገሃነብ ማለት የሰው ልጅ ለማፍቀር/ለመውደድ ያለው ተፈጥሮው በመሰረቁ/በመሟጠጡ የሚገጥመው መከራ/ስቃይ ማለት ነው።›› ይለናል

እውነቱን ልንገራችሁ፤ ወገኖቼ!!

ስለገሃነብ ብዙ ትርጉሞች ሰምቻለሁ እንደእዚህ የገሃነብ ትርጉም ግን አእምሮዬ ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረ የለም። አእምሮዬ ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረው ግን ያለምክንያት አይደለም። በግሌ ለአባባሉ ትልቅ ክብደት እንድሰጥ ያደረገኝ ወያኔ ስልጣን በሃገራችን ከያዘ ጀምሮ በሃገራችን የከፈተው ፈታኝ ዘመን ነው። የወያኔ የዘር ፖለቲካ ስብእናችን እየሰረሰ በአንድ ሃገር ውስጥ የምንኖር ዜጎች አንዳችን በሌላው ጥርጣሬ እንዲኖረን፣ አንዳችን የሌላውን ውበት ማድነቅ፣ የሌላውን ሳቅ መሳቅ የሌላውን ስቃይ መቁሰል በማንችልበት የጥላቻ እስርቤት ውስጥ እየጨመረን ነው የሚል ስጋት ስለሚሰማኝ ነው።

ምንም ነገር እንደራስ ልምድና ተመክሮ አስተማሪነት ያለው ስለማይሆን ይህንን ስጋቴን ለመግለጽ ከራሴ ታሪክ ልነሳ።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2005 ሰኔ ወር ከምርጫው በኋላ፣ ትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ያሉበት የወያኔ ሴኩሪቲ አፋኝ ቡድን ዛሬ በ80 አመቱ ቃሊቲ ወህኒ ቤት የተጣለውን የአባቴን ቤት አጥር ዘሎ ገባ። በግቢ ውስጥ በሚኖረው በርካታ ህዝብ ላይ ሽብር ፈጠረ። እኔን ወደ እስርቤት ሲወስድ፤ እዛው ግቢ ውስጥ ቆሞ ሁኔታውን በሚመለከተው አባቴና ሌሎች በግቢው ንዋሪዎች በሆኑ በርካታ ግለሰቦች ፊት አንዱ በያዘው ዱላ ጀርባየና ማጅራቴ ላይ መታኝ። የገረመኝ ዱላው አልነበረም።

ለምን ትማታለህ? የጠየቃችሁኝ አላደርግም አላልኩ? በማለት በዱላ ለመታኝ፤ በእድሜው ወጣት ለነበረው የወያኔ ሰላይ ጥያቄ አቀረብኩ። ሰውየው የሰጠኝ ምላሽ አስገራሚ ነበር። ከ15 የሚበልጡ ሰዎች እየሰሙት ‹ደብድቡት›› የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶናል ነበር ያለው። ዱላው በእዚህ አላበቃም። አራተኛ ፖሊስ ጣብያ ከተወሰድኩ በኋዋላ ስድስት የደህንነትና የፌደራል ፖሊስ አባላት በዱላ በጠመንጃና በሽጉጥ ሰደፍ ሲቀጠቅጡኝ እርስ በርሳቸው በትግርኛ ቋንቋ እየተናገሩ ነበር። የራሳቸውን ዘር እየቀጠቀጠ የመግዛት መብት እንዳለው፤ ለእዛም መብት ያበቃቸውን የተለየ ጀግንነት የተላበሱ መሆናቸውን በድንፋታ እየተናገሩ ነበር ዱላውን የሚያዘንቡብኝ። በደህና ቀን የተማርኳት ትግርኛ ባለጌ ስድባቸውን ለመስማት አስቻለችኝ። እንደእውነቱ ከሆነ የሰማሁትን ከሰማሁ በኋላ ጆሮየን ቢቆርጡኝ ትግርኛ የማልሰማ ቢሆን ደስ ባለኝ ነበር።

በእዛ እለት በአዲስ አበባ ንጹሃን የህዝብ ደም የሰከሩት የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ሁሉንም ዘር ነበር የሚሳደቡት። ለብሄር እኩልነት ቆሚያለሁ እያለ ከሚነግድ የድርጅት አባላት፤ በአደባባይ እንዲህ አይነቱ ዘረኛ ንቀት ለሁሉም የሃገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ይገለጻል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። በተለይ አማራ ብለው የሚጠሩትን ዘር እጅግ አጸያፊ ከዘር ጋር የተያያዘ፣ እዚህ ለመድገም የሚቀፍ ስድብ እየተሳደቡ ነበር የዱላ የርግጫ የካራቴ ናዳ ያወርዱብኝ የነበረው። ልብ በሉ ዘር የምለው ቃላት ያለምክንያት አይደለም። እነዚህ የወያኔ ሰዎች፣ ሰዎችን በደምና በአጥንታቸው እየቆጠሩ ወገናቸው አድርገው እንደሚያዩ ሁሉ ሌላውንም አጥንቱንና ደሙን መርምረው በዘሩ ጠላት አድርገው የሚፈርጁ ናቸው። ይህ ደግሞ ባለፉት አመታት ድርጊቶቻቸው የበለጠ ገሃድ የወጣ ተፈጥሮአቸው ሆኗልና የሚያከራክር አይደለም።

ወደ ደብዳቢዎቼ ስመለስ ግማሽ ፊቴን በሰደፍ አፍርሰው ኮማ ውስጥ ጨምረውኝ በጭቃ እጨቀየው የፖሊስ ጣቢያው መሬት ላይ ጥለውኝ ሄዱ። በዘር ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ብልግና የሞላውን ድርጊታቸውን የፈጸሙት ከ700 እስከ 800 መቶ የሚሆን እስረኛ ፊት ነው። ዱላው ምንም አላማ አልነበረውም። ጥየቄ የለም። ምንም ነገር የለም። ደብድቡት የሚል ትእዛዝ የተላለፈው በወቅቱ ቅንጅትን በመደገፌ ብቻ ነበር። የኔን መንፈስና ቅስም ለመስበር ነበር። ሌላውንም በአብዛኛው ወጣት የነበረውን እስረኛ ለማሸበር የተደረገ በጭካኔና በእብሪት የተሞላ ድርጊት ነበር።

በድብደባው የተነሳ ስንት ሰአት ወይም ደቂቃ ኮማ ውስጥ እንደቆየሁ አላውቅም። ከኮማ ስወጣ ግን ያገኘሁት ማንነቴ፤ ኮማ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ከነበረኝ ማንነቴ የተለየ ነበር። ለደብዳቢዎቼ ብቻ ሳይሆን ከደብዳቢዎቼ ዘር ጋር ለተገናኘ ማንኛያውም ሰውና ነገር ከፍተኛ ጥላቻና ምሬት ልቤን ሞልቶት አገኘሁት። ከሚደበድቡኝ 6 የመለስ ዜናዊ አሽከሮች በላይ የሚሻገር ከሰዎቹ ትግሬነት ጋር የተሳሰረ ለዘራቸው በሙሉ መጥፎ ስሜት እንዲሰማኝ ያደረገ ጥላቻ ስብእናየን እንደአሲድ ሲበላው አገኘሁት። በጣም የሚያስፈራ የሚያስደነግጥ የሚያሳዝንና የሚያበሳጭ ስሜት ነበር።

በግሌ የማውቀውን የትግራይ እናቶች ደግነትና ሩህሩህነት፣ የትግራይ አርሶ አደር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ከህሊናዬና ከልቤ ፍቆ ማንኛውን ከትግሬነትን ጋር የተያያዘ ነገር በጠላሁበት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ራሴን ከሳትሁበት ሁኔታ የነቃሁት። ይህ ነበር ያሳዘነኝና ያበሳጨኝ። እነዚህ ዘረኞች እኔንም እንደእነሱ ስብእና የሌለው አውሬ ሊደርጉኝ ነው በማለት ነበር የተናደድኩት። እንግዲህ አስቡት እኔ በቅርቡ ብዙ ነገር ስለትግራይ ህዝብ ምንነት የማውቅ ሰው፣ እንዳውም ከደርግ ጥይት ሸሽቴ መጠለያዬ የሆነኝን፣ በኋላም ከረሃብ ከወባ ከተስቦ ተርፌ በህይወት እንድሰነበት በመሃከሉ አኑሮ፣ ከእዛ በችግር ከተሞላ ህይወቱ ያለውን አካፍሎ መልሶ ሰው ያደረገኝን የትግራይ ማህበረሰብ በአንድ ጨፍልቄ ለዘር ማንዘሩ ጥፋት ከተመኘሁ ሌላው የእኔ አይነት የህሊና ወቃሽና አስተዋሽ የሌለው ተመሳሳይ በደል የሚደርስበት ዜጋ ምን ሊያስብ እንደሚችል ገምቱት። በለመስ ዜናዊ የወያኔ ወታደሮች ቤቱ የተቃጠለው፤ የታረደው፣ ሚስቱን ወጣት ሴት ልጁን የተደፈረው፣ መንድሩ የጋየው፣ በገፍ የተጋዘው፣ የተዋረደው፣ የተዘረፈው፣ የዘር ማጥፋት እርምጃ የተወሰደበት መላው የሃገሪቱ ህዝብ ምን ይሰማዋል?

በእዚህ ስራ በዋንኛነት መለስ ዜናዊ የሚያሰማራቸውም የሚያምናቸውም የወያኔ ሰዎች በሙሉ የትግራይ ሰዎች ናቸው። ያው ሁላችሁም በቅርቡ ዝርዝሩን እንዳያችሁት ወታደራዊና የሴኩሪቲ ተቋማቱን በሙሉ የተቆጣጠሩት ወያኔዎች ናቸው። ከእነዚህም መሃል ከሌሎች ብሄሮች የተቀላቀሉ ጥቂት ወታደሮችና ደህንነቶች ቢኖሩም ዋናውን ስልጣን ይዘው ፍለጠው ቁረጠው ግደለው እሰረው ዝርፈው የሚለውን ትእዛዝ የሚያስተላልፉት የትግራይ ተወላጆች የወያኔ አባላት ናቸው።

እነዚህ ሰዎች የሚፈጸሙትን ግፍና አበሳ ሆን ብለው ዘረኛ የሆነ ልባስ ይሰጡታል። ሆን ብለው ስልጣኑ ያለው በእኛ በትግሬዎች እጅ ነው ምን አባክ ትሆናለህ የሚል መልእክት ነው በሁሉም ድርጊቶቻቸው ለማስተላለፍ የሚፈልጉት። ልብ በሉ ስልጣን በእኛ ወያኔዎች እጅ ነው አይሉም። በእኛ በትግሬዎች እጅ ነው የሚሉት። ግፍና በደሉ የሚደርስበት የሃገሪቱ ህዝብ የሚደርስበትን ስቃይ በዘር የተደራጁ ሃይሎች ዘር ለይተው የሚያደርሱበት የዘር ጥቃት አድርጎ እንዲያየው ሆን ብለው ተግተው እየሰሩ ነው። ይህ ጉዳይ ከወታደራዊና ከአፈና ፈርጆች አልፎ በሰልጣንና ሃብት ድልድልም አግጦ የሚታይ ሲሆን ደግሞ ሁኔታው ምን ያህል የከፋና የተወሳሰበ ሊሆን እንደሚችል ገምቱት።

አንዳንድ ሰዎች ይህ ጉዳይ ተደባብሶ አሁን የምሰጠውን ትኩረት አግኝቶ ወይይት እንዲደረግበት አይፈልጉም። በእዚህ እኔ አልስማማም። በበኩሌ ይህ ሽፋፍኖ የመሄድ ጉዳይ የትም አያደርሰንም። እንዳውም በድፍረት በአደባባይ በመነጋገር የወያኔ የዘር ፖለቲካ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ ፈታች ላይ ሳይፈነዳ መፍትሄ እንድንፈልግለት ያሸችለናል ባይ ነኝ። እውነቱን ለመናገር ይህ አይነቱ ዘረኛ አመለካከት፤ የመለስ ዜናዊና የወያኔ አባላት ብቻ ችግር ነው የሚል እምነት የለኝም።

ኋላቀርነትና ድህነት ጠፍረው በያዙት፣ ነጻነትና መብት ባልተከበረበት፣ ህዝብ ከማንኛውም አይነት ጭቆና እራሱን መከላከል የሚችልባቸው የዴሞክራሲና የፍትህ ተቋማት በሌሉበት ሃገር ውስጥ የሚገኝ ኋላቀር ልሂቅና ምሁር ወያኔ ስራ ላይ ባዋለው ተመሳሳይ የዘር ፖለቲካ በቀላሉ ለስልጣንና ለጥቅም እበቃለሁ ብሎ የሚያስብ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

በእኔ አመለካከት የወያኔ ዘረኛ አመለካከትና ደርጊት፤ ሌላው ህዝብ ወገኑ የሆነውን የትግራይን ህዝብ የሚያይበትን አይን ብቻ አይደልም እያቀላ ያለው። ሌሎችም በሃገርቱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰባት ወይም ብሄረሰቦች የየራሳቸውን አክራሪ ዘረኛነት እንዲኖራቸው እያደረገም ነው። ሰዎች ከራሳቸው ዘር ውጭ ሌላውን ማመን የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እየገቡ ለመሆናቸው በርካታ ማስረጃዎች አሉ። በጋራ ሁላችንም በሰውነታችን ብቻ ልንቀበላቸው የሚገቡ፣ ዘርን፤ ቋንቋንና ባህልን ተሻግረው ሊያስተሳስሩን የሚገቡ ጉዳዮችን፤ ለምሳሌ ውበትን፣ ፍትህንና እውነትን የመሳሰሉ ቁም ነገሮች፣ ትርጉም የሚኖራቸው በዘር መነጽር እስካየናቸው ብቻ የሆነበት ሁኔታ ውስጥ እየገባን ነው። ይህ ደግሞ ቀደም ብዩ የጠቀስኩትን ዶስቶቭስኪ የገለጻውን ገሃነብ በሃገራችን መገንባት ጀምረናል ማለት ነው።

**ይቀጥላል**

## ወያኔ ለአገዛዙ ታማኝ አልሆኑም ያላቸውን

ክገጽ 1 የዞረ

የወያኔ አገዛዝ በፖሊሶች ላይ ብቻ ሳይሆን በመከላከያ ሰራዊቱም ላይ ተመሳሳይ ደባ እንደሚፈጽም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ከእነብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ና ከግንቦት 7 ጋር ንክኪ አላቸው እየተባሉ በርካታ የሰራዊት አባላት ለእስር እየተዳረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎአል። በርካታ የመከላከያ ሰራዊት አባላትም እየከዱ ወደ ኤርትራ እንደሚኮበልሉ ከመከላከያ አካባቢ የደረሰን ዜና ያመለክታል። ሰሞኑን ወደ ኤርትሪያ የኮበለሉ ሶስት ወታደሮች፣ ሞሀመድ ሱሌይማን ነገዎ፣ አለምሸት ዘመንፈስቁዱስና ዘላለም እጅጉ ለኤርትሪያ ሬዲዮ እንደገለጹት አገዛዙ በሰራዊቱ ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ በከፋ መልኩ ቀጥሎአል። በርካታ የሰራዊት አባላትም ለመኮብለል ሁኔታዎችን እያመቻቹ እንደሚገኙ ወታደሮች ገልጸዋል።

\በተያያዘ ዜናም የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ አገዛዝ እጅግ በመማረሩ የግንቦት 7ትን ነጻ አውጭ ሀይል በተስፋ እንደሚጠባበቅ የአዲስ አበባ ዘጋቢያችን ገልጿል።

ህዝቡ ባገሪቱ ውስጥ በሚታየው ምስቅልቅሉ የወጣ የኑሮ ሁኔታና የሙብት አፈና እጅግ በመማረሩ፣ አገዛዙን በሀይል ለማስወገድ የሚፋለሙ ወገኖችን ለመርዳት ሙሉ ዝግጁነት እንዳለው ሪፖርተራችን ገልጿል።

ባሁኑ ጊዜ ጥቂቶች በተንደላቀቀ ኑሮ ውስጥ እየኖሩ አብዛኛው ህዝብ ግን የሚበላው አጥቶ እንደሚሰቃይ የተናገረው ዘጋቢያችን፣ ይህም ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ምስቅልቅል ሊፈጥር እንደሚችል ግምቱን አስፍሯል።

## ወያኔ የሃሰት ምስክሮችን ሚስጥር ያወጣሉ በሚል

ክገጽ 1 የዞረ

በሌላ በኩል መረጃው "ወያኔ ፕሮፌሰር አስራትን በመርዝ ለመግደል ሲያስብ ተንኮሉ የተጠነሰሰው ለረዥም ጊዜ በባልቻ ሆስፒታል ውስጥ በቋሚነት ታካሚያቸው የነበረን፤ በኢህአፓ ወገቡን በጥይት እሩምታ ተመቶ ከደርግ ግዜ ጀምሮ ማለቂያ የሌለው ኦፕሬሽን የተደረገለትንና ኑሮውን በሆስፒታሉ ውስጥ ያደረገውን ሃገር የሚያውቀውን በሽተኛ በመጠቀም እንደነበር አውስቷል።

‹‹ፕሮፌሰሩ ይህን ከደርግ ግዜ ጀምሮ ወደ ወያኔ ዘመን የተሸጋገረውን ህመምተኛ አዘውትረው መጠየቅ ልምድ እንደነበራቸው›› መረጃው ጠቅሶ ፕሮፌሰር ሁሌም በጉብኝት ወቅታቸው ከእዚህ በሽተኛ ጋር ሻይ የሚጠጡ መሆኑን የተገነዘበው የወያኔ የደህንነት ክፍል በሽተኛው የበርካታ አመታት ሃኪሙ በነበሩት በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ የሻይ ብርጭቆ ውስጥ መርዝ ከቶ አንዲገላቸው ሃስብ አቅርቦለት እንደነበር ይገልጻል፡፡

ሆኖም በሽተኛው ለሃኪሙ በነበረው ፍቅርና ታማኝነት የወያኔ ወንጅል ተባባሪ አልሆንም ብሎ አሻፈረኝ በማለቱ የወያኔ የመርዝ ግድያ ተንኮል ለጊዜው በተግባር ሳይውል ቀርቷል ይላል፡፡

መረጃው ዘገባውን ሲያጠቃልል በሃገራችን የመንገስታት ታሪክ አንደመለስ አገዛዝ ዐይነት መንግሰት የተባለውን ተቋም ያዋረደ እንዲሁም በማፍያ ነፍሰ ገዳዮችና ወንጀለኛ ድርጅቶች ስልት የሚመራ አገዛዝ ታይቶ አይታወቅም ብላል።

በወያኔ ሸንገላ በሃሰት የሚመሰክሩ ግለሰቦች ህዝብንና ፈጣሪያቸውን ባይፈሩ አንኳን በሃሰት ከመሰከሩ በኋላ ምስጢር ያወጣሉ በሚል ራሱ ወያኔ መልሶ ሊያጠፋቸው እንደሚችል ከጎጃም አርሶ አደሮች ትምህርት ወስደው ውሎ አድሮ በህዝብና በፈጣሪ ፊት ሊያስጠይቃቸው የሚችል ወንጀልና ሃጥያት ከመፈጸም ሊገቱ ይገባል ሲል አሳስቧል፡፡

## በኢትዮጵያ የተፈጠረው የሀይል እጥረት ለወያኔ

ክገጽ 1 የዞረ

በህዝብ ዘንድ "የጨለማ ባለስልጣን"የሚል ቅጥያ ያተረፈው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣንም፡-ዘላቂ መፍትሄ ማመላከት ተስኖት" ችግሩ እስከማቃልለው ድረስ ጄኔቴተር እየገዛችሁ ተጠቀሙ " የሚል ያልተከፈለበት ማስታወቂያ ደጋግሞ በማስተጋባት - የነአዜብን ገበያ በስፋት ማሻሻጥ ከጀመረ እንደሰነበተ ባለስልጣኑ ተናግረዋል፡፡

የሀይል እጥረቱን ተከትሎ በአገዛዙ ቁንጮ ቤተ-ሰቦች በስፋት እየተፈፀመ ያለው ዘግናኝ ሙስና፡-"ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" የሚያሰኝ ነው ያሉት እኚሁ ባለስልጣን፤የኢትዮጵያ ህዝብ በጨለማ ተውጦ በረሀብ በሚሰቃይበት ጊዜ እየተፈፀመ ያለው ቡድናዊ ዝርፊያ ተባብሶ መቀጠሉ-ሰው ሆኖ መፈጠርን የሚያስጠላ ነው ብለዋል።

ከፀጉር ማስተካከያዎች እስከ ሆቴሎችና ኮሌጆች ያሉት ተቋማት የሚጠቀሟቸው ትናንሽና መካከለኛ ጉልበት ጄኔረተሮች ምን ያህል ነጃጅ እየፈጁ እንደሆነ መረጃውን ለማጠናቀር ጥረት እያደረጉ እንደሆነ የገለፁት ባለስልጣኑ፤ሆኖም በአጠቃላይ ከፍተኛ ወጪ እየወጣ እንደሆነ መገመቱ ቀላል ነው ብለዋል፡፡

"..ከዚህም ባሻገር "ይላሉ ባለስልጣኑ ".... ከዚህም ባሻገር እያካሄዱት ካለው ቡድናዊ ቢዝነስ በተጓዳኝ ድንገት ኢትዮጵያ ውስጥ የኤሌክትሪክ ችግር ቢቃለል በሚል ሃሳብ- ራሳቸው የሸጧቸውን ጄኔሬተሮችን በቅናሽ ገዝተው መልሰው የሚሸጡበን አገር እያፈላለጉ መሆናቸው በተጨባጭ መረጃ ተረጋግጧል"

## ዶናልድ ፔይን ፕሬዚዳንት አባማ ለአምባገነኑ

ክገጽ 1 የዞረ

የቡሽ አስተዳደር ይከተል የነበረውን የተሳሳተ ፖሊሲ የኦባማ አስተዳደርም እየተገበረው እንደሚገኝ የተናገሩት ሚ/ር ፔይን፣ ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በዲሞክራሲ መብቶች መከበር ዙሪያ እንዲያጠነጥንም መክረዋል። በኡጋዴንና በሌሎች ቦታዎችም የሚደረጉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ማብቃት እንዳለበት ያስረዱት ኮንግረስ ማን ፔይን፣ የኦባማ አስተዳደር ለመለስ ዜናዊ ማስጠንቀቂያ ይልካል ብለው ተስፋ እያደረጉ መሆኑንም ተናግረዋል።

ኮንግረስ ማኑ ኢትዮጵያውያን በአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሲገደሉ፣ ሲታሰሩና ሲሰቃዩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆማቸውን በተለያዩ ጊዜዎች ያረጋገጡ ሲሆን፣ በዚህ ሥራቸውም በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ አድናቆትንና ከበሬታን አግኝተዋል።

ኮንግረስ ማን ፔይን እና የአውሮፓ ኅብረት የፓርላማ አባል የሆኑት ተወዳጇ አና ማሪያ ጎሜዝ ከግንቦት 1997 ምርጫ በኋላ የወያኔን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በጽኑ በመታገላቸው፣ ኢትዮጵያ በፋሽሽት ኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት ከፍተኛ ተጋድሎ ካደረጉት ከእነ ሲልቪያ ፓንክረስት ተርታ እንደሚያስመድባቸው ብዙዎች ይስማማሉ።

## እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ መታሰር በርካታ

ክገጽ 1 የዞረ

ግንቦት 7 ያጠናቀረው ተጨባጭ መረጃ እንደሚያመለክተው ብአዴንን የወያኔ የአማርኛ ዲፓርተመንት አድርገው ለማስተዳደር ወያኔ በምስለኔነት ከመደባቸው በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት የድርጅቱ መሪዎች በስተቀር አብዛኞቹ የብአዴን አባላትና በርካታ ከፍተኛ ካድሬዎች ጭምር "በቃን ለወያኔ" በማለት ራሳቸውንና ድርጅታቸውን ከወያኔ ምስለኔዎች ነጻ ለማውጣት በከፍተኛ እልህ እየተንቀሳቀሱ ነው።

እንደ መረጃው ከሆነ እነዚህ የብአዴን አባላት በህዝብ በኩልም ትልቅ ግፊትና "በርቱ ከጎናችሁ ነን" የሚል ድጋፍ እየጎረፈላቸው ነው።ይህ በእንዲህ እንዳለ በብአዴን አባላት ዘንድ የተቀጣጠለው የነፃነት ትግል በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ሰደድ እሣት ወደ ኦሮሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ውስጥ ዘልቆ መግባቱ ተረጋግጧል።

እንደ ግንቦት ሰባት ተጨባጭ መረጃ እጅግ በርካታ የኦህዴድ አባላትም ድርጅታቸውን የኦሮሞን ህዝብ ለሆዳቸው ከሸጡ ከነምናሴ ገብረህይወት ወይም መለስ በሰጠው የመጋለቢያ ስም ከሚታወቀው ከአባዱላና ከጓደኞቹ ነፃ በማውጣት እና ከነኢህዴን-ብአዴን ጋር በመተባበር "ወያኔን ከኢህአዴግ ማባረር" በሚል መሪ የትግል ሀሳብ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

ሆኖም የግንቦት 7 የፖለቲካ ዲፓርትመንት "አባላቱ ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት እየተከተሉ ያለውን ውስጣዊ የትግል እንቅስቃሴ ስልት ከመግለፅ ተቆጥቧል

## የውያኔ ሹመኞች በየሄዱበት አገር መክዳት የአገዛዙ የመጨርሻ ሰዓት መድረሱን አመላካች ነው

ክገጽ 1 የዞረ

ግንቦት ሰባት የውስጥ ምንጮች በሰጡት አስተያዬት በውጭ ምንዛሬ እጥረት ሳቢያ ሹመኞች የውጭ አገር ጉዞ እንዳይደርጉ ሰርኩላር ባይተላለፍ ኖሮ እጅግ በርካታ ባለስልጣኖች "ጀምበሯ አዘቅዝቃ ሳትጠልቅ - ራሳቸውን ከከፋ ወንጀለኛ በመለየት በኩል" በነ ኤርምያስ መንገድ ሲሄዱ ባየናቸው ነበር ብለዋል።

የዘረኛው የመለስ አገዛዝ በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ከወደቀ ወዲህና በቅርብ ጊዘ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገብኝ ካላ ወዲህ የስርዐቱ እድሜ እያጠረ መምጣቱን የሚያመለክት መሆኑ ከተጠያቂነት ለመሸሽ ከሀገር በተለያየ ምክንያት ለመውጣት እድል ያገኙ የወያኔ ባለስልጣን በሙሉ መሸሽ መጀመራቸው ታውቀል። የመለስ ዜናዊ ስልጣን እለቃለሁ ብሎ ማውጅ እየተሸረሸር ለመጣው ስልጣኑ የገጠመው ፈተና አመልካች ነው በማለት ብርካታ ባለስልጣናት አስቀድመው ለመጥፋት እያሰቡ እንድሆነ የግንቦት ሰባት የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

የግንቦት ሰባት ለፍትህ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንኢናቄ ሊቀ-መንበር ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በተደጋጋሚ ባደረጓቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች "ወያኔ ላይ ላዩን ስታዩት ትልቅ መንግስት ሊመስላችሁ ይችላል፤ ሆኖም እናንተ እንደምትገምቱት ትልቅ ሳይሆን የተፍረከረከ፤ ውስጡ ባዶና እጅግ ደካማ የዱርዬዎች ቡድን መሆኑን አረጋግጥላችኋለሁ" ማለታቸው ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org